# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ

## ትንሣኤ በዋለ በአራተኛው ሰንበት የሚከናወን ሥርዓተ አምልኮ

ዘመነ ትንሣኤ ወይም ፋሲካ የሚባለው ከጌታችን ትንሣኤ ጀምሮ እስከ ዕርገት ያሉት ቀኖች ናቸው። በእነዚህ ዕለታትና ሳምንታት የሚዘመሩት መዝሙራት ሞትን ትንሣኤን ስቅለትን የመሳሰሉትን የሚያነሱ ናቸው።

### የዕለቱ ምስባክ

አንሰ ሰከብኩ ወኖምኩ
ወተንሣእኩ እስመ እግዚአብሔር አንሥአኒ
ኢይፈርህ እም አእላፍ አህዛብ

እኔ ተኛሁ አንቀላፋሁም
እግዚአብሔርም ደግፎኛልና ነቃሁ
ከከበቡኝ ከአእላፍ ሕዝብ አልፈራም

መዝ ፫፤፭-፮

ትርጉም፦ ሦስት መአልት ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር አደርኩ እግዚአብሔር አንስቶኛልና ተነሳሁ እንጂ (ሉቃ ፳፬፤፴፳)

(አብ አስነሳው፣ መንፈስ ቅዱስም አስነሳው፣ በስልጣኑ ተነሳ የሚሉ አባባሎች ሁሉ አንድ ናቸው፤ የመለኮታዊ አንድነታቸውን የሚያመለክቱ ናቸው።)

ወንጌል፦ ሉቃስ ፳፬፤፴፫-፴፭
ቅዳሴ፦ የዲዮስቆሮስ ቅዳሴ (እምቅድመ ዓለም)

### የዕለቱ ቅዱስ ያሬድ መዝሙር ርዕስ

ተንስአ ወአንስአ ኲሎ ሙታን
«ተነሳ ሙታንን ሁሉ አስነሳ»

### በቅዳሴ ሰዓት የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች

| | ንባብ | አንባቢ |
|---|---|---|
| 1 | ቄላ ፫፤፩-ፍጻሜ | ዲያቆን (ገባሬ ሰናዩ) |
| 2 | ፩ኛ ጴጥ ፫፤፲፰-ፍጻሜ | ዲያቆን (ንፍቅ ዲ.) |
| 3 | የሐዋ ሥራ ፲፩፤፩-፲፱ | ረዳቱ ቄስ (ንፍቅ ካህን) |

### የዕለቱ ትምህርት

## «ተነሳ ሙታንንም አስነሳ»

ቅዱስ ያሬድ ስለ ክርስቶስ ትንሣኤ ማራኪ በሆኑ መንፈሳውያን ቃላት እንዲህ በማለት ዘመረ። «ክርስቶስ ተነሳ ሙታንንም አስነሳ፣ እስረኞችን ፈታቸው (አዝ) በታላቅ ኃይልና ስልጣን ነፍሳትን ነፃ አወጣ (አዝ) አልአዛርን ተነስ ያለው፣ እውሩን በቃሉ የፈወሰው፣ ሞትን ድል አድርጎ ተነሳ (አዝ) ትንሣኤውን በሰንበት አደረገ፣ በሦስተኛው ዕለት ተነሳ ሙታንንም እስነሳ» ብሎ ዘመረ።

በአርባእቱም፦ «አምላክ ሞያ ለሞት ወጼሐ ለነ ፍኖተ ጽድቅ ወሕይወት እግዚአ ለሰንበት ተንስአ ለነ»
ትርጉም፦ «አምላክ ምትን ድል ነሳው የሕይወትና የጽድቅ መንገድን ጠረገልን የሰንበት ጌታ ተነሳልን» አለ።

ከዚህ የቀሩትን የቅዱስ ያሬድ የመዝሙር ቃላት በትምህርቱ መጨረሻ በጥቅስ መንገድ ተዘጋጅቷል። በኲር ሆኖም ተነስቷናል። የኤማሆስ መንገደኞች ወደ ኢየሩሳሌም በሄዱበት ወቅት ሐዋርያት «ጌታ በእውነት ተነስቷል ለስምዖንም ታይቷል» እያሉ ነበር ያገኟቸው። አይሁድ እንዳስወሩት ሳይሆን ጌታ በእውነት ተነስቷል። ዛሬ በተነበበው ወንጌል ከዚህም ሌላ በዝግ ቤት ገብቶ ትንሣኤውን ገለጠ፤ ሰላሙን ሰጥቶ ተማሪዎቹን የትንሣኤው ምስክሮች እንዳደረጋቸው እናነባለን (ሉቃ ፳፬፤፴፫-፴፬)። ክርስቶስ እንደተነሳ ሙታንንም አስነስቷል፤ ያስነሳል። መጽሐፍ ቅዱስ የክርስቶስ ሞት ሞታችን፣ ትንሣኤውም ትንሣኤያችን እንደሆነ ያስተምረናል። በሃይማኖት እንደምንነሳም እርግጠኞች ስለሆንን እንደምንነሳና በተስፋ እንደተነሳን እናምናለን። ቅዱስ ጳውሎስ «እንግዲህ ከክርስቶስ ጋር ከተነሳችሁ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ ያለበትን በላይ ያለውን አስቡ» ይለናል (ቄላ ፫፤፩-፪)። እንዲህም ከሙታን ባስነሳው በእግዚአብሔር አሰራር በማመናችሁ ከእርሱ ጋር ተነሳችሁ» አለ (ቄላ ፪፤፲፪)። በኤፌሶን መልእክቱም «የጸጋውን ባለጸግነት ያሳይ ዘንድ ከእርሱ ጋር አስነሳን» አለ። ቤተ ክርስቲያንም ትንሣኤ ልቦና ተነስታለች። በእምነትም መነሳትዋን ትቀበላለች (ራዕ ፳፤፬-፮)። የክርስቶስ ትንሣኤ የእሷ መሆኑን በማመን ቤተ ክርስቲያን «ከሞት አትነሽም»፤ «የመቃብር ኃይልም አልተሻረልሽም፣ አትነሽም» ብለው መናፍቃን ቢቃወሟት እንዲህ በማለት ትመልሳለች። «መጽሐፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለኃጢአታችን ሞተ ተቀበረም፣ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሳ … ክርስቶስ ከሙታን እንደተነሳ የሚሰበክ ከሆነ ከእናንተ አንዳንዶቹ ትንሣኤ ሙታን የለም ለምን ይላሉ? ትንሣኤ ሙታንስ ከሌለ ክርስቶስም አልተነሳም፣ ክርስቶስም ካልተነሳ ስብከታችን ከንቱ ነው፤ እምነታችን ደግሞ ከንቱ ናት?» ብላ ትመልሳለች። በተጨማሪም ከቁጥር ፳፱ እስከ ፶፰ ይመልከቱ። በታላቁ ጉባኤዋም «ወተንስአ እሙታን በከመ ጽሑፍ ወስተ ቅዱሳት መጻሕፍት» (በቅዱሳት መጽሐፍ እንደተጻፈ ከሙታን ተለይቶ ተነሳ … ) ብላለች። በማጠቃለያም «ወንሴፎ ትንሣኤ ሙታን ወሕይወተ ዘይመጽእ ለዓለመ ዓለም» (የሙታንንም መነሳት ተስፋ እናደርጋለን የሚመጣውንም ሕይወት ለዘለዓለም) ብላለች።

### ጥቅሶች

ግዕዝ፦ ለአህዛብ ምክሆሙ ለጻድቃን ሞገሶሙ ለድኩማን ጽንአሙ ወልድ ዋህድ ምያ ለሞት ገብረ ትንሣኤ በሰንበት (ቅዱስ ያሬድ)
አማርኛ፦ ለሕዝቦች መመኪያቸው፣ ለጻድቃን ሞገሳቸው፣ ለድኩማን ጽንአታቸው አንድ ልጅ ሞትን ድል ነሣው ትንሣኤውን በሰንበት አደረገ።

ግዕዝ፦ ተንስአ ክርስቶስ እሙታን ከይዶ መቃብሪሁ ለአዳም ወበትንሣኤሁ ገብረ ለነ ሰላመ ለጻድቃን አብርሀ (ቅዱስ ያሬድ)
አማርኛ፦ የአዳምን መቃብር ረግጦ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ተነሳ ለጻድቃን አበራ ሰላምን አደረገልን።

ግዕዝ፦ በሞቱ አንስአ ሙታነ ሲኦለ ወሪደ አርአየ ሙስና ረከብነ ሕይወተ በትንሣኤሁ (ቅዱስ ያሬድ)
አማርኛ፦ በሞቱ ሙታንን አስነሳ፣ ሲኦል ወርዶ ጥፋትን ደመሰሰ በትንሣኤው ሕይወትን አገኘን።

ስብሐት ለእግዚአብሔር … አሜን።